# ያመት በዓል ገበያ ቅኝት

ይሄይስ አእምሮ

እንኳዋን ለአዲሱ ዓመት ማለትም ለፋሲካው በዓል በሠላም አደረሳችሁ፡፡ ይሄ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም የአነጋገር ዘይቤ አንዳንዴ ልብ ሳልለው ስንቅር ይልብኛል እናንተ ሆዬ፡፡ መንጌ በል ሲለው በመስቀል አደባባይ ዓመታዊም ይሁን ሞቅታዊ ሰሞነኛ ንግግሩ ‹ ውድ አባቶቼ፣ ውድ እናቶቼ፣ ጉዋድ እህቶቼና ወንድሞቼ፣ በጠቅላላው ውድ የሀገሬ ጉዶች ማለትም ጉዋዶች! … እንኳዋን ለአምስተኛው ማለትም ለአሣረኛው ማለትም አስረኛው የአብዮታችን በዓል ደረሳችሁ!› ሊለን ይችል ነበር፡፡ ምን እንዲህ ብቻ - ‹ አንዳንድ ፀረ-አብዮታውያን ማለትም አብዮታውያን ባደረጉት ቆራጥ ተጋድሎ ጠላቶቻችንን አኩርተን ማለትም አሣፍረን ወደመጡበት መልሰናቸዋል፤ ለራት ሲያስቡንም ምሳ አድርገናቸዋል፡፡ በዚህ አሣፋሪ ማለትም አኩሪ ተግባርም ታላቁ አብዮታችን ከአጥቂነት ማለትም ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት መሸጋገሩን ሳበሥር ሀዘን ማለትም ደስታ ይሰማኛል፡፡› ልንባልም እንችል እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ለነገሩ ወደዚያ ምን ወሰደኝ? አነሳሴ እንደወትሮው ሁሉ ስለወቅቱ የገበያ ዳሰሳ ማለትም ቅኝት ጥቂት ነገር ጣል ለማድረግ ነበር፡፡ አይ የትዝታ ነገር! ምነው መንጌን አሁን ባገኘሁት? ኦሮሞ ምን ብሎ ይተርታል አሉ፤ ‹ ይበጃል ቢሉን አህያ አረድን፤ ተመልሰው አይበጃችሁምና ወዲያ ጣሉት ቢሉን ጠራርገን ጣልን፤ ለሦስተኛ ጊዜም - እንዴ? ምን ነካችሁ ይበጃችሁ ነበር እኮ ቢሉንና ወደጣልንበት ሥፍራ ሄደን ብንፈልገው አጣነው፡፡› ግሩም አባባል! የፊተኛው እየናፈቀን፣ የአሁኑ በጥላቻ እያንገሸገሸን፣ የበስተፊታችን በሥጋትና በፍርሃት ቆፈን እያቆራመደን የምንኖር ምሥኪን ሕዝብ መሆናችንን ይህ ወርቃማ ምሳሌያዊ ንግግር ይጠቁማል፡፡ እስኪ ደግማችሁ አጢኑት፡፡

ለነገሩ በዓመት በዓል አካባቢ ጥንትም ቢሆን በሸቀጦችና በዕርድ ከብቶች ላይ መጠነኛ የዋጋ ለውጦች መኖራቸው ያለ ነው፡፡ ሆኖም በዓላቱና ግርግሩ ሲያልፉ ዋጋ ተረጋግቶ ወደነበረበት ይመለሳል እንጂ በጀመረው ጉዞ ቀጥሎ ሕዝብን ለምሬት አይዳርግም፡፡ አሁን በወያኔ ዘመን ግን የአንድን ዕቃ ዋጋ ለሰው እዬተናገርክ ባለህበት ቅጽበት ራሱ ከምትገምተው በላይ ነው ዋጋው ጨምሮ የምታገኘው፡፡ ወዴት እያመራን እንደሆነ ፈጣሪ ይወቀው፡፡ እናም ዋጋ ስትናገር አንተም ፈርቅ መያዝ የሚኖርብህ ጊዜ አለ፡፡ አንዱዋ ‹ ሰላም ካልኩህስ በሁዋላ ሰላም ነህ ወይ?› በማለት ጉዋደኛዋን እንዳደናገረችው ዓይነት መሆኑ ነው፡፡

የሰሞኑም ሆነ የምንጊዜውም ወያኔያዊ ገበያችን ከቁጥጥራችን እንደወጣ ነው፡፡ የግንባታ ዕቃዎችን ነገር መተው ነው፡፡ እሱ የኛ የሚሊዮኖች ችግር አይደለም - እዬዬም ሲደላ ነው አሉ ዕንባ የሚወጣው፡፡ የኛ ችግር የዝንጀሮዋ ‹ቀድሞ የመቀመጫዬን ነገር› ያለችው ዓይነት ነው - ‹ቀድሞ የሆዳችን ነገር› ለማለት ፈልጌ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆድ አሣር እያበላ ነው አሁን - ለአንዳንዶቻችን ቤት የመሥራት ጣጣ ስንተኛ ብቻ በህልም መልክ እየመጣ ያባንነን እንደሆነ እንጂ ለብዙኃኑ ተራ ቅዠትና ቅብዠር ከመሆንም ካለፈ ቆይቶኣል፡፡ አንድ ኩንታል ስሚንቶ አምስት መቶ ብር ተገዝቶ፣ አንድ የባለ16 ሜትር ኪዩብ ጭነት አሸዋ በ4000 ብር (ፈርቅ ይዤ 5000 ልበለው ይሆን?) ተገዝቶ፤ አንድ የባለ12 ቁጥር የአርማታ ብረት(ፌሮ) ከብር 150 በላይ ተገዝቶ . . . የትኛው ኢትዮጵያዊ ቤት ለመሥራት እንደሚያልም ማለትም እንደሚቃዠ ይታያችሁ፡፡ አሁን ቤት የሚሠሩት የሀገርን መሬት እንደልባቸው ከየማዘጋጃ ቤቶች በሙስናና ለፖለቲካው ባላቸው ቀረቤታ ሳቢያ እንደፈለጉ እየወሰዱ የተወሰኑትን በመሸጥ በተወሰኑት ላይ ደግሞ ሕንጻዎችን በመገንባት የሚያከራዩ ወገኖችና መዝባሪ ወንድምና እህቶቻችን ናቸው፡፡ ከዲያስፖራውም ወዳገራቸው ተመልሰው የግንባታ ሥራዎችን

የሚያካሂዱ ሞልተዋል። በነዚህ የግንባታ እንቅስቃሴዎችና በብድርና በምጽዋት በተገኘ የበጀት ድጋፍ በሚሠሩ መንገዶች ታይታ ምክንያት እኛ ብዙኃኑ ደልቶንና ፖለቲካውም ተመችቶን የምንኖር የምንመስላቸው ቂላቂል ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ሰዎች በተለይም ዲፕሎማቶች መኖራቸው አይካድም፤ በዚህ ሽውራራ አካሄድ ክፉኛ እተጎዳን ነን። የወቅቱ ሁኔታ የሚያሳየው ተጨባጭ እውነት ግና ‹ፀጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል› ዓይነት ነው። በሕይወት ያለን እንመስላለን ግን ሞተናል፤ ቀባሪ ጠፍቶ እንጂ። እርግጥ ነው የቁም ተዝካር ይወጣል። በቁም የሞተን መቅበር ግን በተለይ ባገራችን የተለመደ ባለመሆኑ በወያኔው የግፍ አገዛዝ በቁማችን የሞትነውን በስልሳና ሰባዎቹ ሚሊዮናት የምንቆጠር ዜጎችን ደፍሮ የሚቀብር የአስቀባሪ ድርጅትም ሆነ መያድ አጥተን እንጂ እኛስ ‹አልሞትንም ብለን አንዋሽም›። በስማም - እንዲያው ለነገሩ ግን እኛ ኢትዮጵያውያን በታሪካችን ውስጥ እንደዚህ ተጨካክነን እናውቅ ይሆን ለመሆኑ? በሚገርም ሁኔታ ያለውንና የሌለውን ዜጋ የሀብት ልዩነት ስታጤኑ እኮ የሰማይና መሬት ርቀት ራሱ አይገልጸውም። ሀብታሙን ያን ሁሉ ገንዘብ ከየት አምጥቶ አግበሰበሰው ትላላችሁ። ድሃውን ደግሞ እንዲህ አጥቶ ነጥቶ አጠገቡ ያለውንና በንግድ ስምም ይሁን በተለያየ የሙስናና የንቅዘት መንገድ አላግባብ ያካበተውን ገንዘብ እንደጉድ የሚረጨውን ሀብታም እያየ ጫፉንም ሳይነካው በ‹ማሽላ ሲያር ይስቅ› ዓይነት ያንጀት ያልሆነ ፈገግታ ታጅቦ በርሃብ ማለቁን ስትመለከቱ በርግጥም ኢትዮጵያ ተዓምረኛ ሀገር መሆንዋን ትገነዘባላችሁ። አዎ! እንደኛ ተዓምረኛና በተዓምር መሽቶ የሚነጋለት ተዓምረኛ ዜጋ በዓለም ቀርቶ በዩኒቨርስ ቢፈለግ ጭራሹን አይገኝም።

ከሰሞኑ ፈረሰኛ ያመት ባል ዋጋዎች ለ‹መዝናናት› ያህል ቀጣዮቹን ልግለጽና ይብቃኝ - ለምን ልንጨርጨር። እንዴ ጨጉዋራችን ተልጦ፣ ቆሽታችን አርሮ፣ አንጀታችንም ነድዶ አለቅን እኮ ጎበዝ! ምን ይሻለን ይሆን?

1. ለበቀደሙ የፋሲካ በዓል ለእርድ ከቀረቡ ቅልብ በሬዎች መካከል ከብር 25000 በላይ ተጠርቶ በ25000 ብር እንደተሸጠ ከሁነኛ ሰው ሰምቻለሁ።( እንዳትደነግጡ ልላ ሳይሆን ሃያ አምስት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ነው ያልኩት) ይህ በሬ መቼም የራስ ዳሸንን ተራራ ያህል መግዘፍ አለበት!
2. አንድ የበግ ሙክት ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ተጠርቶ ወደዚያው አካባቢ ተሸጦኣል።
3. አንድ ወንድ እርግብ እሚያህል ዶሮ የቀዳም ሥዑር ዕለት ማታ ላይ ራሴው ጠይቄ 180 ብር በመባሌ ተውኩትና በቤቴ የአፍንጫ ነስር እንዋን ባቅሙ ኮርቶብኝ ምንም ደም ሳላይ በዓሉ አልፎኣል። መቼም ግፍ ነው ደም ሳያዩ በዓልን ማለፍ!
4. አንድ ኪሎ ቅቤ ከ‹ኖርማል› መሸጫው ባንዴ ተምዘግዝጎ 200ብር ሲደፍን ሃይ ያለው ጤናማ መንግሥትም ሆነ አእምሮ ያለው ነጋዴ አልነበረም።
5. አንድ ሊትር ፈሳሽ ዘይት(ያልታሸገ/ከበርሜል የሚቀዳ) ከብር 45 ተሽቀንጥሮ በኢትዮጵያውያንና/ት ዘይቶች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ 60 ብር የገባው በዚህ ሰሞኑ የትንሣኤ ዋዜማ አካባቢ ነው። ከዚህ በሁዋላም ማን እንደሚያወርደው ገና የምናየው ይሆናል። የታሸገውና ከበቆሎ ተሠራ የሚባለው አንድ ሊትር ዘይት ደግሞ ብር110 ብቻ! በነገራችን ላይ የአሁኑ ዘመን የገበያ ዋጋ አባዜ ሲሰቀልና እንደመንኮራኩር ሽቅብ ሲወነጨፍ እንጂ ሲወርድ አለመስተዋሉ ነው። የሚገርም ተጠየቃዊ አካሄድ። ይህ ደግሞ በኛ ሀገር ብቻ የተከሰተ ኩዋሻርኩዋራዊና ቤሪቤሪያዊ የጨነገፈ ሀገራዊና ሕዝባዊ ዕድገት ምልክት ይመስለኛል፤ እንዲያውም ነው - የምን ዳር ዳርታ ነው።

6. አንድ ኪሎ ሥጋ ከሉካንዳ ለመግዛት ስትሄድ ሉካንደኛው በሞቀ ሰላምታ ይቀበልህና በጆሮህ ‹በመንግሥት ወይንስ በኛ ላድርግልህ› ይልሃል፡፡ በነሱ ካልክ ከፈለግኸው ይቆረጥልሃል - ብትፈልግ ከሻኛው - ቢሻህ ከዳቢቱ - ቢያሰኝህ ከወርቹ - ከፈለግህም ከሽንፍላው፤ ዋናው ያንተ ፍላጎት መከበሩ ላይ ነው፡፡ በመንግሥት ካልክ ግን ሉካንደኛው እግዜርን ካልፈራ እንዴት እንደተጫወተብህ እንኳዋን ሳታውቀው በጋዜጣ ጠቅልሎ የሰጠህን ‹ሥጋ› እቤትህ እተከበረችው ውድ የሰማንያም ትሁን የአርባ ባለቤትህና ምናልባትም አማቶችህ ፊት ስትከፍተው ሁለቱ የበሬው ቆለጦችና ቢያንስ አንድኛው ጆሮው በጣፊያ መሰል የቆዳ ሥጋ ተጠቅልሎ ልታገኝበት ትችላለህ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለ የብልግና ማለትም የብልጽግናና የዕድገት ደረጃ ላይ ተደርሶኣል፡፡ እናስ? እናማ ለዚህ ዕድገትና ብልጽግናችን ስንል በፊታችን እሁድ የሚዘከረውን የዳግማይ ትንሣኤን ሌላ የቂጣ በዓል ምክንያት በማድረግ ጽዋችንን እናንሳና  ከፋሲካው ዋና በዓል የተረፈችን ቅራሪ ቢጤ በጉዋዳችን ካለችን እሱዋን እየተጎነጨን ከ‹ህዳሴው የአባይ ግድብ፣ ከብልሁና አስተዋዩ ቅንድቡም ከሚያምረው ጠ/ሚኒስትራችን ብልጥ ማለትም ብልጣብልጥ አመራር ጋር ወደፊት - ፉልድረት - - ን(ä)ቅድሚት› እንበላ!፡፡ በቃ! ለአሁኑ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ማንኛውም አስተያየትዎ ለዚህ ዘባራቂ ሰውዬ ዕንቁ ነው! [yiheyisaemro@gmail.com]